# ኤርትራንም፡ ሞቃዲሾንም፡ ማንንም መጠቀም አለብን

ከጠላት መማርን አሜን ብለው የማይቀበሉ ብዙዎች ናቸው። አይዋጥላቸውም። ሰው እንዴት ከጠላቱ ይማራል? መማር ካለብን ከማንም ለመማር መዘጋጀት አለብን። በተለይ ካሸነፉን ጠላቶቻችን መማር አለብን። ለማሸነፍም ላለመሸነፍም። እነሱ ያሸነፉበትን መንገድ ጠንቅቀን ካላወቅን፡ አናሸንፋቸውም። አንዱ ኢህአዴግ እኛን ያሸነፈበት መንገድ ከማናቸውም የኛ ጠላቶች ጋር መወገኑ ነው። ከጠላቶቻችን ጋር ሁሉ ወግኖ ወጋን። ረታንም። ከኢህአዴግ ጠላቶች በሙሉ መወገን አለብን። ሳንመርጥ ሳናማርጥ። ማለቴ፡ ጥያቄው መሆን ያለበት፡ እያንዳንዱን የጠላቴን ጠላት እንዴት ልጠቀምበት ነው እንጂ፡ የለም የጠላቴ ጠላት የኔም ጠላት ነበርና ወይንም ነውምና ከሱ አልወግንም ማለት አያዋጣም። ሁለት የሌላ ጠላቶችን ጠላት የሚያሳስብ (ይጠብቃል፡ ልክ እንደ ስበት) የጠላትነት የስበት ህግ አለ። ማንም ጠላት የጠላቱን ጠላት ይፈልገዋል። እኛም እንፈልጋቸዋለን፡ እነሱም ይፈልጉናል። ይሄ የጠላትነት መግነጢሳዊ ህግ ፍጹምና ዘላለማዊ ነው ብለን ባንከራከርም፡ ለጊዜው ለዘመናት የዓለምን የጠላትነት ሕግ የገዛ ዓብይ ህግ ነው። እኛም ከዓለም ሕግጋት ውጪ አይደለንም። ይሄ አንደኛው ነው።

ሁለተኛ፡ ታጋይ አይኮራም። ማለታችን፡ ታጋይ የሚያዋጣው ካዋጣው እዚያው ሄዶ ያገኘዋል እንጂ፡ የሚያዋጣኝ እዚህ ይምጣ ብሎ ተጀንኖ አይቀመጥም። ኢትዮጵያን ከጠቀመ እኛም የማናደርግበት ምክንያት የለም። አስመራ፡ ብድግ ብላ፡ እሷ ጉያ እንድንገባ እንድትለማመጠን፡ ያለፈ አጀንዳዋን ሁሉ ርግፍ አድርጋ እንድትተው፡ እንደውም እንድትጸጸትና ይቅርታ እንድትጠይቅ ሁሉ የሚፈልጉ አሉ። ኖ ኖ እንደዚያ አይሆንም። ኤርትራ አነሰም በዛም፡ አረረም መረረም፡  ግራም ነፈሰ ቀኝ አገር ነች። ብዙ ደም አፍሳ አገር የሆነች አገር ነች። እኛ ደግሞ ገና አስራ ምናምን ዓመት መሬት የምንድህ ምንም የሌለን የሀሳብ ታጋዮች ነን። ስለዚህ እኛ እንጂ ወደ ኤርትራ መሄድና ያሉትን እድሎች መርምረን መጠቀም ያለብን፡ ኤረትራ አይደለችም እኛ እግር ላይ ወድቃ፡ ይሄን አደርግላች   ኋለሁ፡ ይሄን እለውጣለሁ፡ ይሄንንም አሻሽላለሁ ማለት ያለባት። መጥምቁ ዮሃንስ ወደክርስትቶስ እንዲመጣ ወይንስ ክርስቶስ ወደመጥምቁ ዮሀንስ እንዲሄድ ሳታውቁ ቀርታችሁ ነውን? ከኤርትራ ልንጠቀም የምንችለው ቅንጣት ታክልም ነገር ካለ፡ ያንን መርምሮ መጠቀም የኛ ፋንታ ነው። ጠላት እያንዳንዷን ጥቃቅን እድል እየተጠቀመ ነው እዚህ የደረሰው። ከሱዳን ጋር፡ ከግብጽ ጋር፡ ከአሜሪካ ጋር። አልቃኢዳ በዚያን ግዜ ቢኖር ከአልቃኢዳም ጋር ከመጠቀም ወደኋላ አይልም፡ ጠላት። ዛሬም ያንን ነው የሚያደርገው። የሆኖ ሆኖ፡ እነዚህን ጠላቶቻችንን ለመደምሰስ፡ እንኩዋንስ ከአስመራ፡ ከሞቃዲሾም እንገጥማለን።